# የቅንጅት ፋና

የቅንጅት ፋና በራ እንደገና
ገና ብዙ ገና መች አበቃና
የበፊት ድላችን ይደገማልና
ቆራጥ ኢትዮጵያዊ በአቋምህ ጽና።

ገና ከጠዋቱ ገና ከጅምር
ጠላትና ወገን በጅምላ ድምር
ተደባልቆ ኖሮ ሳይጠረጠር
እንቅፋት ቢሆንም አፈንጋጭ አጥር
ተነቅሎ ተጥሏል እሾህ አሜኬላው
ፈሪና ወላዋይ ከሃዲና ባንዳው።

መሠረቱ የጸና በኢትዮጵያ ሕዝብ
ነጥሮ ጠርቶ ወጥቷል ወገን አታስብ
ቅንጅትን ተስፋ ነው አየነው ሲያብብ።

የቅንጅት ፋና በራ እንደገና
ገና ብዙ ገና መች አበቃና
የበፊት ድላችን ይደገማልና
ቆራጥ ኢትዮጵያዊ በአቋምህ ጽና።

የሰኔና ጥቅምት ሰማዕታት ሁሉ
ደም መና አይቀርም ዋጋ ለከፈሉ
ፍራያቸው አብቧል አገር ወገን ያሉ
እስራት ድብደባ መከራና እንግልት
ከሥራ መባረር በሽታ ስደት
ዕጣ ፈንታው ሆኖ ለመብቱ ቢሟገት
አሸናፊው እሱ ነው ቀኑ የደረሰ ለት።

ጠላት ብዙ ሰርቶ ኃይሉን ለማጥፋት
በእግዚአብሔር ቸርነት በሕዝቡ ጸሎት
በሽተኛው ድኖ ሕዝብን ለመምራት
ይኸው ቆሟል ዛሬ በሁላችን ፊት።

ለጀግናው መሪያችን ምስጋና ይድረስህ
ትዕግሥትና ጽናት ቆራጥ አመራርህ
ለዚህ አብቅቶታል ደስ ብሎታል ሕዝብህ።

ከትግራይ ጀምሮ ጎንደር፣ ጎጃም፣ ወሎ
ወለጋና ሸዋን አሩሲን አካሎ
ባሌና ሲዳሞ፣ ሐረርጌና ከፋ
ኢሉባቡር መቱ እንዲሁም ጎሙጎፋ
ከአራቱም ማዕዘን በርረው ተጉዘው
አዲስ አበባ ላይ ጉባኤ አድርገው
ቅንጅት አንድ ነው
አንድ ሕዝብ ነን ብለው
ኢትዮጵያዊነትን አጠናክረው ይዘው
ጠላትን ድል መቱ እጅ ለእጅ ተያይዘው

ወጣትና ሴቱን በደንብ አደራጅቶ
አዲሱም አመራር ሁሉንም አካትቶ
ለሥራ ተነስቷል የለም እንቶ ፈንቶ።

እናንት ቡቃያዎች የሞረሽ ወጣቶች
ወገንን ቀስቃሾች ሕዝብን አስደሳቾች
ታሪክ መዝግቦታል ምን እንደሰራችሁ
በርቱልን እናንተ እግዜር ይባርካችሁ።

ከተማ ገጠርም አገር ቤትም ላላችሁ
አሜሪካ አውሮፓ ካናዳ ያላችሁ
አውስትራሊያ አፍሪካም ሆናችሁ
ድጋፍ ያሰማችሁ መልዕክት የላካችሁ
ቅንጅት ደጋፊ እንኳን ደስ ያላችሁ።
የእኛ ድርሻ ደግሞ ምን ይሆናል ቢባል
እነርሱ መርዳት ነው ያለማወላወል
ሕዝቡ አንድ ሆኖ መሪውም ተነስቷል
ከዚህ በላይ ዜና እረ ምን ይመጣል
ድርሻችንን ደግሞ መወጣት ይገባል።

የቅንጅት ፋና በራ እንደገና
ገና ብዙ ገና መች ተነካና
የበፊት ድላችን ይደገማልና
ቆራጥ ኢትዮጵያዊ በአቋምህ ጽና።

ከአሸናፊ
ቶሮንቶ፤ ካናዳ
ሰኔ 17 ቀን 2000 ዓ.ም